# የወጣቶች የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት

# (Youth Savings Account Service)

## 1. መግቢያ

የወጣቶች የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት ማለት ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 24 ዓመት ለሚሆናቸው ወጣቶች በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት ነው። አገልግሎቱ በተጠቀሰው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የቁጠባ ባህልን እንዲያዳብሩ፣ ገንዘባቸውን በዕቅድ እንዲጠቀሙ እና ከባንክ አገልግሎት ጋር በወጣትነት ዕድሜያቸው እንዲተዋወቁ ይረዳል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እነዚህ ወጣቶች ቁጠባን ከወዲሁ የየእለት ኑሮአቸው አካል በማድረግ ብልህ፣ ኃላፊነት የሚሰማቸው እና በአጠቃላይ የወደፊት ተስፋ የሰነቁ ባለራዕይ ወጣቶች እንዲሆኑ ለማስቻል ይህን አገልግሎት አዘጋጅቷል።

## 2. የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች

ከ 18- 24 ዓመት እድሜ ያላቸው

- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወጣት ተማሪዎች፤
- በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወጣቶች፤
- የቀን ሠራተኞች፤
- የታክሲ ሾፌሮችና ረዳቶቻቸው፤
- ነጋዴዎች፤
- የቤት ሠራተኞች፤

- የግንባታ ሠራተኞችንና ሌሎች ከላይ በተጠቀሰው የዕድሜ ገድብ ውስጥ ያሉ ወጣቶችን ያጠቃልላል።

## 3. የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎቱ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች

- ✓ የነገ አገር ተረካቢ ለሆኑ ወጣቶች የገንዘብ አጠቃቀምን በማስተማር ጥሩ ዜጋን ማፍራት ያስችላል፤
- ✓ ወጣቶች የኃላፊነት ስሜት ተሰምቷቸው ኑሮአቸውን በራሳቸው እንዲመሩ የገንዘብ አያያዝ ነፃነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
- ✓ ወጣቶች ከባንኩ ጋር ደንበኝነት በመመሥረት ወደፊት ዘላቂነት ያለው የንግድ ትስስር እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
- ✓ ሠርተው የሚቋጥሯትን ገንዘብ በአግባቡ ማስቀመጥ ያልቻሉ እና በጥንቃቄ መቆጠብ ተስኗቸው ገንዘባቸው ለዝርፊያ፣ ለቅሚያ እና ለብክነት የተጋለጠባቸውን አምራች ወጣቶች ወደ ባንክ በማምጣት ገንዘባቸውን በጥንቃቄ እንዲያስቀምጡና እንዲቆጥቡ ያስችላል፤
- ✓ የቁጠባን ባህል አዳብረው ለወደፊቱ ቅርስ እንዲያፈሩ ያስችላል፤
- ✓ ገንዘባቸውን በሱስ እና በሌሎች አላስፈላጊ ነገሮች ላይ ከማዋል በመቆጠብ ወጣቶች ጤናማ፣ አምራችና ባለራዕይ እንዲሆኑ ያግዛል፤
- ✓ ለትምህርት፣ ለጤና እና ለማኅበራዊ ኑሮአቸው በቂ ገንዘብ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
- ✓ ወጣቶች በነፃነት ራስን የመምራት ክህሎት እንዲያዳብሩ ብሎም የአመራር ክህሎት እንዲኖራቸው ይረዳል፤
- ✓ ራሳቸውን ለሚያስተዳድሩ ወጣቶች በራሳቸው የተሳካ ኑሮን መምራት እንዲለመዱ ያግዛል፤
- ✓ የተለያየ የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ድጋፌ በማጣት ራሳቸውን ለመቻል በተለያየ ዓይነት የጎዳና ላይ ንግድ ወይም አገልግሎት ወይም በጊዜያዊ ቅጥር አገልግሎት እየሰጡ የሚያገኟትን ገንዘብ አብቃቅተው ለመቆጠብ እንዳይችሉ ወደ ባንክ መምጣት ለነሱ የማይገባ እየመሰላቸው

ገንዘባቸውን ለብክነት ያጋለጡ ዜጎችን ወደ ባንክ በማምጣት ገንዘባቸውን በአግባቡ እንዲቆጥቡ ያደርጋል፤

- ✓ ወጣቶች የከፍተኛ ትምህርት እንዲከታተሉ እና የሙያ እድገት እንዲያደርጉ የገንዘብ ምንጭ ለመፍጠር ያስችላል፤
- ✓ የሚያገኟትን ጥሪት በመቆጠብ አሁን ካሉበት ወደ ተሻለ ንግድ ሥራ እንዲገቡ ያስችላል፤

## 4. የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎቱ የሚያስገኛቸው ልዩ ጥቅሞች

- ✓ የዚህ ሂሳብ ተጠቃሚ ወጣቶች ባንኩ ለሌሎች የቁጠባ ሂሳቦች ከሚሰጠው የተሻለ የወለድ መጠን ያገኛሉ፤
- ✓ የኢንተርኔት እና የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎትን በነፃ ያገኛሉ፤
- ✓ ስለሂሳባቸው የሚጠይቁትን ዝርዝር የሂሳብ እንቅስቃሴ መግለጫ (statement)ያለክፍያ ያገኛሉ፤
- ✓ ከሂሳባቸው ወደሌላ ለሚልኩት ሃዋላ ከመደበኛ የኮሚሽን ክፍያ ቅናሽ ያገኛሉ።

## 5. የቁጠባ ሂሳቡን ለመክፈት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

- ➢ ዕድሜው ከ18 እስከ 24 ዓመት ለመሆኑ ከሚኖርበት አካባቢ አስተዳደር የታደሰ መታወቂያ ማቅረብ፤
- ➢ ስድስት ወር ያልሞላው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶግራፍ ማቅረብ፤
- ➢ ሂሳቡን ያለተቀማጭ ገንዘብ(zero balance) መክፈት ይቻላል ነገር ግን ሂሳቡ በተከፈተ በ 30 ቀናት ውስጥ ቢያንስ ብር 25 ( ሃያ አምስት) ተቀማጭ ካልተደረገ ሂሳቡ ይዘጋል።

በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በወጣቶች ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚደግፏቸውን ወጣቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በማድረግ ባለራዕይ የሆኑ ታዳጊ ወጣቶችን እንዲያፈሩ ያበረታታል።

**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ**

የወጣቶች የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት

**ስልክ ቁጥር**:- 251-11-122-87-87

251-11-551-50-04

**ፋክስ ቁጥር**:- 251 -11-122-86-06

**ፖ.ሣ. ቁጥር**:- 255

**ኢሜይል**:-cbecomu@combanketh.et

**ስዊፍት ኮድ**:-CBETETAA

**ድረ-ገጽ**:-www. combanketh.et